# ውሾቹና ግመሉ

አብርሃም በየነ

“ውሾቹ ይጮሃሉ፤ ግመሉ ጉዞውን ቀጥሎአል”
ይህን የዐረብ ተረት እንዲህ ይዘግቡታል፤

የታሪክ ስርወ-መሰረቱን
ገልበው ሲያዩት ተረቱን፤

ከጥንት ጀምሮ ስናውቀው ዐመሉ
በጥቁር ህዝቦች ለምጥ ዜና መዋዕሉ
ድሮም ባሪያ ፈንጋይ ነበረ ግመሉ፤

ህዝብ ዘርፎ ሲጉዋዝ ሌባ በግመሉ
ስርቆቱን ለማስቆም ውሾች ይጮሃሉ፤

ለምንስ አይጮሁ?

ይጮሃሉ በዕርግጥ፤ ከበው ይጮሃሉ
በህብረት አዋክበው ጭነቱን ሊያስጥሉ።

## ራስ ዳሸን

ጋይንት ደብረ ታቦር ደንቢያና ፎገራ
አለፋ ጣቁሳ አርማጭሆ ቁዋራ
አዳኝ አገር ጫቆ ሰሜን ጃናሞራ
ወልቃይት ጠገዴ ወንዙ አይደፈሬ
ሊቦ ወይና ደጋ ፀለምት እስከ ዛሬ
ወይ ደረስጌ ማርያም በየዳ ወይ አንጎት
ውቤን ዳግም ወልዶ ሰው መሆን ተስኖት
ዳሸንን ትግሬ አርጉዋል በሽንፈቱ ፍኖት።
ህዳር 2004

EthioLion.Com